ጋለሪያ ቶሞካ ግርማ ሰቦቃን ያቀርባል

GALLERIA TO.MO.CA. PRESENTS Girma Seboka



# ጥበባዊ ፍቅር Artistic Passion

## የሥዕል ትርዒት Art Exhibition

ጥር 23 2006 ዓ.ም. January 31/2014

(የፊት ሽፋን)
አምዳዊ ድርሰት

(On the cover)
Verical Composition

January 31/2014
Presented by Galleria TO.MO.CA.
Art Director - Eshetu Tiruneh
Managing Editor - Mifta Zeleke
Editor in Chief - Nebiyu Girma
Printed by Central Printing Press

ይዘት

ጥበባዊ ፍቅር እና ስሜት ፫
ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ ፲

Contents

Artistic Passion & Emotion 3
Girma Seboka 10

# ጤና ይስጥልን!

የሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ 'ጥበባዊ ፍቅር' የተሰኘውን የሥዕል ትርዒት ጋለሪያ ቶሞካ አቀረበላችሁ። የሥዕል ትርዒቱ ሠዓሊው ስለሕብረተሰባችን ያለውን እሳቤና ስሜት በሥራው ያንጸባረቀበት ነው። ለስድስት ሳምንታት የሚቆየው ይህ የሥዕል ትርዒት ስለማኅበረሰባችንና ስለሥነ-ጥበባችን ያለንን ምልከታ የምናሰፋበት ነው:: በጋለሪያ ቶሞካ የምታጣጥሙት ኢትዮጵያዊ ቡና ከትርዒቱ ጋር ደስታ ያብዛላችሁ!

# Dear All,

Welcome to the colorful show of 'Artistic Passion' by painter Girma Seboka. The show is believed to render a perspective to grasp the artist's thoughts, feelings and understanding towards our society. The show stays for six weeks in entertaining, creating insight and of course a new artistic perspective. Enjoy the show along with the ever appealing Ethiopian coffee in Galleria TO.MO.CA's coffee bar.

# ጥበባዊ ፍቅር እና ስሜት፤

ራሱን ጥበብ ለጥበብ የወለደና ያሳደገ ፤ራሱንም በጥበብ የፈለገና በማግኘት ላይ ያለ ጎልማሳ ሠዓሊ አለ ከተባለ ግርማ ሰቦቃ አንዱ ነው፡፡በአዲስ አበባ በ1968 ዓ.ም የተወለደውና ያደገው፤በእቴጌ መነን አንደኛ ደረጃን በአየር ጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተማረው ግርማ ሰቦቃ ፤ከተግባረ እድ ትምህርት ቤት ደግሞ በ1984 ዓ.ም በድራፍቲንግ ሞያ በሰርቲፊኬት ተመርቋል፡፡በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤትም በተመረቀበት ሙያ ለሁለት ዓመታት ተቀጥሮ ሠርቷል፡፡

ራሱን በጥበብ ውስጥ ለመውለድና ጥበብን ለመፈለግ ስነበረው ታላቅ ሕልምና ምኞት ለመገዛት፤ወደ ቀድሞ የአዲስ አበባ ሥነጥበብ ትምህርት ቤት ተብሎ የሚጠራውና፤ዛሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አለ ፈለገ ሰላም ሥነጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት በተባለው በመግባትና በመማር ፤በ1995 ዓ.ም በኪነ ቅብ ሙያ ለመመረቅ ችሏል፡፡ ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ ከተመረቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁኑ ድረስ ባለፉት አሥርና አሥራ አንድ ዓመታት ከዘጠኝ ያላነሱ የግል ከአሥራ አምስት ያላነሱ የቡድን ሥዕል ትርዒቶችን አሳይቷል ፡፡ የተንዘበት መንገድ ዛሬ ካለበት ነባራዊ ሁኔታና ከሥዕል መምህርነቱ ጋር ሲታይ ከፍተኛ ዕውቀታዊና ክሂሎታዊ ልምዶችን አካብቶበታል፡፡

ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ፤ በጋለሪያ ቶሞካ ያቀረባቸው ኪነ ሥዕላት፤ ባለፉት አሥርና አሥራ አንድ ዓመታት ትጋትና ጥረት በተመላበት ጥበባዊ ፍቅርና ስሜት እየተቀሰቀሰና እየተንቀሳቀሰ ባካበተው ልምድ፤ ራሱን በራሱ ያገኘበትን፤ ግላዊ የጥበብ አቅጣጫ የቀየሰበትን፤ ግላዊ የጥበብ ዘይቤ የተለመበትን

# Artistic Passion and Emotion

One of the grown-up artists who constructed, explored and found himself within art is Girma Seboka.He was born in Addis Ababa in 1961. He completed his primary and secondary education in Menen Asfaw and Ayer Tena High Schools respectively. He also graduated in certificate in Drafting from Addis Ababa Technical School in 1992. He worked in the field for two years in the Municipality of Addis Ababa.

To make his dreams conceivable, he went to study in the former Addis Ababa Fine Arts School (the present Addis Ababa University Alle Felege Selam School of Fine Arts and Design) and he graduated in painting in 2003. In the past eleven years, he participated in nine solo and fifteen group exhibitions. In his present circumstances along with his profession in art teaching, he is an artist of immense skills and experience.

The artworks of Girma Seboka featured in Galleria TO.MO.CA are the accruals of his passion for gallant artistic search, encounter and experience. Hence, the show can be taken as the reflection of the recollection of his self discovery in the artistic direction he projected

የድምር የጥበብ ውጤቶች ነፀብራቅ ናቸው፡፡ ይበልጡን ድብልቅ ቁስ ጥበባትን /mixed media/ የሚጠቀመው ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ ፣ ንጥር ሕብረ ቀለማትን ፣ ክሮችን ፣ ገመዶችን ፣ ጆንያዎችን ፣ ቀለማዊ ጨርቆችን ፣ ወዘተ በተናጠልና በማደባለቅ በበፍታ ሰሌዳው ላይ በመለጠፍ፣ በመስፋት ፈጠራዊ ስሜቱን ይገልጻል፡፡የጥበብ አቅጣጫው ከፊል ምስላዊ ወይም ከፊል ኢ ምስላዊ /semi-figurative or semi- abstract / የሚከተል ሆኖ አቀራረቡም ዝይብ ኪነ ቅቦች /stylized paintings/ ናቸው፡፡ ድርሰታዊ አደረጃጀቱም ሲበዛ ዓምዳዊና ድርድራዊ ዝርጎች በጌጣዊ ሽልሞች የተደራጁ ቅንብሮች ናቸው ፡፡ ለምሣሌ፣ በዚህ የሥዕል ትርዒት ውስጥ ከቀረቡት ኪነ ቅቦች መካከል፡-

ሀ. “ዓምዳዊ ድርሰቶች” ፣ “ የከተማው ድባብ”፣ “ ባጃጅ በከተማው ውስጥ “፣ “ሞቃት ቀን” ፣ የመሳሰሉትን ኪነ ቦች ፣ በአትኩሮት ላዩ፣ ሳስተዋለና ሳገናዘበ ተመልካች ከፊል ምስላዊ ወይም ከፊል ኢ ምስላዊ አቀባቦች መሆናቸውን በቀላሉ መገመትና መለዮት ይቻላል ፡፡

ለ.ዘይቤያዊ ኪነ ቅብነቱን /stylized paintings/ በጌጣዊና ንቅሳዊ(motifs) የአቀባብ ስልት ላይ የመሠረተው ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ፣ከሥዕል መገለጫ ቋንቋ ውስጥ ይበልጥ የሚጠቀምባቸው ፀናሥራት፣መስመሮች ፣የቀለማዊ መስመሮችና የቁሳዊ ገመድ መስመሮች ሲሆኑ ፣ “ዓምዳዊ ድርሰቶች” ፣ “ እናትና ልጅ’’ “ርእስ አልባን” ኪነ ሥዕላት ልብ ይሏል፡፡ ዝርጎች ወይም ጠርዘ ዝርጎች ደግሞ እንዲሁ ጠፍጣፋና ዝርግ ቀለማዊ ቅቦችና ቁሳዊ ኪነ ልጥፍ (montage) ጆንያዎችና ጉብታማ ኪነ ቅርጾች (flat and relief shapes)


Girma Seboka Adey 2003

and the style he meant to achieve. Mostly, he uses mixed media by either combining or disjointing materials like threads, fiber sack, spray, ropes, colorful textiles, flat and relief shapes ...etc on a canvas. He follows semi-figurative or semi abstract artistic direction in



Girma Seboka   Hot Day   2003

ሲሆኑ “ወይዛዝርት በከተማው ውስጥ” “እናትና ልጅ” የሚባሉትን ኪነ ቅቦች ይመለከቷል ። ሻካልሴዎች (textures) በተመለከተ “ ዓምዳዊ ድርሰቶች “ “ወይዛዝርት በከተማው ውስጥ” እና “ርእስ አልባን” ያገናዝቧል ። ሕብረ ቀለሞች (colors) (ሞቃትና ቀዝቃዛ)በአንጻራዊነትና በኅባሬነት ተቀናጅተውና ተቀናብረው በኹሉም ኪነ ሥዕላት ውስጥ ይታያሉ ።



Girma Seboka Ladies in the City 2003

the vista of stylized painting. His composition is more of vertically paralleled flats arranged in decorative motifs. The following points are apparent in his paintings.

A. Vertical Composition: The paintings like "Impressions of the City", "Bajaj in the City", "Balmy Day", and others are either semi-figurative or semi abstract.

B. Stylized Paintings: The motifs (as his stylized painting) based Girma uses elements of art like lines, colored lines and rope lines (refer to the paintings "Vertical Composition", "Mother and Child" and "Untitled"), Planes, flats, montage, fiber sacks and flat and relief shapes (refer the paintings "Ladies in the City", and "Mother and Child") are also used in his works. Texture is portrayed in "Vertical Composition", "Ladies in the City" and "Untitled". In his works of art, colors (warm and cool) are arranged in relative harmony and integration.

The content of his works pats the everyday life of the society and the city metaphorically. Like simple symbolic representation of the ancient cave art using flat shapes and silhouette, he portrayed the present day fashion of tight dressing (which appears to be unlimited by



Girma Seboka  Inside the Jegol  2003

በሥዕላዊ ይዘቱና ርእስ ጉዳዮቹ የጎብረተ ሰቡን የዕለት ሕይወትንና የከተማ ድባብን በዕይታዊ ቋንቋ እያወዛ ዘይቤያዊነቱን ጠብቆ ዳስሷል ። በተለይም ሐረሪን ፣ ፀሐያማ ሙቀትን፣ ገበያን የእናትና ልጅ ፍቅርን ፣እንዲሁም የዘመኑ ሔዋኖች ከወጣት እስከ አዛውንት አንድና እኩል ያደረገውን ወይም መሳ ቅጥ ያጣውን የታይት አለባበስ በቀላሉና በተምሳሌታዊነት ወክሎ እንደ ጥንታዊ የዋሻ ውስጥ ኪነ ሥዕላት በጠርዘ ዝርግነትና በውጫዊ ጠርዝ (shapes or silhouette) ምስል በግሩም ሁኔታ ዘመናዊነቱን እንደ ጠበቀ ገልጾታል።

የሠዓሊ ግርማ ሰቦቃን ኪነ ሥዕላት ለመገንዘብና ለማድነቅ ግድ የሚለን አንድ ጉዳይ አለ ። ከተለመደውና ከመደበኛው የዕለታዊ ሥዕል አመለካከት ወጣ ማለትና በተረጋጋ መንፈስ የሥዕላዊ ቋንቋውን አገላለጽና የድርሰታዊ ቅንብሩን መረዳት፣ ደጋግሞና መላልሶም ማየት፣ ጥበባዊ ጣዕሙንም ማጣጣም ታላቅ ደስታን ያጎናጽፋል።

ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ መልካም የፈጠራ ጥበባዊ ዓመት እንዲሆንለት፣ ቶሞካ ቤተ ሥዕል ማሳያ ጠንካራ የጥበብ ፍቅሩን ይዞ እንዲቆይ፣ ተመልካቹ ራሱን በቶሞካ ጣዕመ ቡናና በሥዕላቱ እየተዝናና እንዲደሰት ከልብ እየተመኘሁ በዚሁ እሰናበታለሁ።

እሸቱ ጥሩነህ /ሠዓሊ/

ጥር፣ 2006 ዓ.ም.

age) in modern style (refer to "Harari", "Sunny Warmth" "Market" "The Passion of mother and Child" and "The Modern Eve"). Understanding the composition and the expression of the elements of the painting in modest mood; and the deviation from the normal visual art indulgence enables us to appreciate and realize Girma Seboka's artworks. Watching all these repeatedly and enjoying the artistic taste grants tranquility.

I wish Girma to have a successful year full of artistic ingenuity, TO.MO.CA to remain with its fervent passion for the art and the audience to keep on enjoying TO.MO.CA's Coffee and the exhibition.

Eshetu Tiruneh

/Painter/
January 2014



Girma Seboka Vertical Experiment 2003



# ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ

በአዲስ አበባ የጦር ኃይሎች ካምፕ ጀርባና ከልደታ ቤተክርስቲያን ጓሮ መሃል ባለች መንደር የተወለደ ሰው ምን ዓይነት የልጅነት ጊዜ ሊኖረው እንደሚችል ገምቱ፡፡ በ1960ዎቹ የነበረውን የከተማውን ድባብ ደግሞ የመቼቱ አካል አድርጋችሁ አስቡት፡፡ ከመንደሩ በስተደቡብ ሲጓዝ ጠብ ጠብ ያሉ መኖሪያ ቤቶች፣ የቀድመው አየር ማረፊያ (ኦልድ ኤርፖርት)፣ ሰፋፊ ሜዳዎች፣ ከሩቅ የሚጣሩት የፉሪ ጋራና ሸንተረሮች የዓይኑ መስሕብ ናቸው፡፡ ወደ ልደታ ሲዘልቅ ደግሞ የሰዎች ትርምስ፣ የተሽከርካሪው ጥድፊያ፣ የደራው የ“ቢሪሞ” ገበያና የቀለጠው የከተማ ሕይወት ቀልቡን መግዛታቸው ግልጽ ነው፡ ፡ በዚህ ዓውድ ያደገ ልጅ ሠዓሊ የመሆን ዕድል ሲያገኝ ሊያንጸባርቅ የሚችለውን ማንነት ለመገመት የኋላ ታሪኩ ፍንጭ የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡ አጅግ ተጠጋግተው ችምችም ያሉና አንዳንዴም በተንና ዘና ያሉ ሥዕላዊ ድርሰቶቹ የሠዓሊ ግርማ ሰቦቃን ጥበባዊ አሻራ ተወልዶ ካደገበትና አሁንም ከሚኖርበት አካባቢ አንጻር እንድንቃኝ እድል ይሰጠናል፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ግላዊ ስሜቶቹና፤ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች የተመሰጦው ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡

ከግርማ ጋር ስናወጋ ማንነቱንና ሕይወቱን ለማወቅ የሚረዱ ነጥቦች

# Girma Seboka

Imagine the childhood of a boy who is brought up in a Addis Ababa in between the backyard of the Lideta Church and the Military Camp of Tor Hayloch. The context and atmosphere of the city in last years of the ninety sixties is also part of the setting. To the south of the village, there are scattered residencies, the old airport, vast fields and the beautiful mountains of Furi allures the eyes. On the other hand, the hectic traffic, interaction of the people and the intense Birimo market are the features that one can attain in Lideta. If nurtured in such milieu, since the background provides essential clues, we can presume the type of identity that one reflects in the art if there is a chance to become an artist. Pronounced details and spacious compositions that Girma uses enable us to understand his art from the vista of his background where he was born, raised and where he is still living. His personal feelings; social, economic and political issues are also depicted in his works.

Here are some points that relieve us to be familiar with the works and life of Girma Seboka. Girma says "The world is full of positive and negative entities. The sacrifice we carry on to live our preferred life determines our destination. My works are depictions of my inner feeling and thoughts". Here is also his response to the question on why he uses exaggerated figures and words

መሃል ጥቂቱን ሳካፍላችሁ፡፡ “ዓለማችን መልካም የሆኑና መልካም ያልሆኑ ነገሮችን እኩል ታስተናግዳለች - ምርጫው የእኛ ነው፡፡ ስመረጥነው ሕይወትና ማንነት የምንከፍለው መስዋዕትነት መድረሻችንን ይወስነዋል፡፡ ስራዎቼ ደግሞ በየጊዜው የማስበውንና የሚሰማኝን የማንጸባርቅባቸው እስትንፋሶቼ ናቸው፡፡” በማለት ሲያጫውተኝ በተጋነነ መልኩ ረዣዥም አድርጐ የሚሰራቸው ምስሎችና “ነፃነት”ና “አዲስ ዘመን” የሚሉ ጽሑፎች ከምን ጋር እንደሚዛመዱ ጠየቅኩት፡፡

“አብዛኞቹ ምስሎች በሐረርና በዙሪያዋ ባሉ ገበያዎች ላይ ያጠነጥናሉ፡ ፡ በዚያ አካባቢ ያሉ ሴቶች ፍጹም ነፃና ነፃነታቸውን በተለያየ መልኩ የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ ይህን ለማጉላት ሞቃት ቀለማትን፣ ቋሚ ሥዕላዊ ድርሰትና ማጋነን (ማግዘፍ) እጠቀማለሁ፡፡ ነፃነትና አዲስ ዘመን እኔም ሆንኩ አብዛኛው የሰው ልጅ የሚናፍቃቸው ነገሮች በመሆናቸው ህሊናዬን ይገዙታል፡፡ እናም በሥራዎቼ አልፎ አልፎ ብቅ ማለታቸው አልቀረም” በማለት ያስረዳል፡፡

ግርማ ለሙዚቃ በተለይም ለጃዝ ከፍተኛ አድናቆትና ፍቅር አለው፡፡ ማስተማር ስራው ቢሆንም እንደትርፍ ጊዜ መዝናኛውም ይደሰትበታል፡ ፡ ምክንያቱ ደግሞ “ማስተማር ነገሮችን ከተማሪዎች ዕይታ አንጻር ሌላ ነገር እንድንማር ማስቻሉ” እንደሆነ ይናገራል፡፡  ሠዓሊ ግርማ ሰቦቃ ባለትዳርና የአንድ ልጅ አባት ነው፡፡

የሠዓሊ ግርማ ሰቦቃን ጥበባዊ ማንነትና ሕይወት ለመዳሰስ ይህ ጽሑፍ እጅግ ቁንጽል ነው፡፡ በግልና ከጋለሪኣ ቶሞካ ባልደረቦቼ ጋር ስቱዲዮውን ስጐበኝና ስለተለያዩ ነገሮች ስንጫወት ያስተዋልኩት ሙያዊና ግለሰባዊ ሥነ ስርዓት ጥንቁቅነትና ጽናት ሩቅ ተሻጋሪ ስኬቱን አመላካች ናቸው፡፡ ስኬቱ እንዲቃና መልካም ምኞቴ ነው፡፡

ሚፍታ ዘለቀ

ጥር 2006 ዓ.ም

like 'Netsanet' and 'Addis Zemen' ('Freedom' and 'New Era' respectively). He answers, "Most of my paintings are based on the life of the markets around Harar. Women in that area constitute free spirited soul. They even reveal their freedom in various ways. I apply warm colors, vertical composition and embellishment. Since freedom and new era are crazes that we all need to have, they sometimes appear in my works".

Girma adores jazz music. Though teaching (he is teaching in Abyssinia School of Art and Design since 2003) is his profession too, he also considers it as leisure. He explains the motive in relation to the fact that teaching grants the opportunity to view things from the students' point of view which gives another dimension to your career. Artist Girma Seboka has a family and he is a father of a son.

This short article is too fleeting to expose the life and vocation of Girma Seboka. However, there is a point to mention about the artist's forthcoming achievements; and this is foreshadowed by his meticulous personal and professional discipline that I noticed in his studio(with my Galleria TO.MO.CA colleagues and alone ) and during the different occasion we met. I wish Girma a successful artistic journey.

Mifta Zeleke

January 2014

ጋለሪያ ቶሞካ

# ግርማ ሰቦቃን ያቀርባል

GALLERIA TO.MO.CA. PRESENTS **Girma Seboka**




Girma Seboka Untitled - 2013

ጋለሪያ ቶሞካ
አድራሻ ሳር ቤት
ከካናዳ ኤንባሲ ፊት ለፊት

Galleria TO.MO.CA
Location; Sar Bet
In front of Canadian Embassy
www.galleriatomoca.com